# የኢትዮጵያዊያን
# አንድነት ዕድር መተዳደሪያ ደንብ

Mailing Address
7052 Santa Teresa Blvd #105
San Jose, Ca 95139

ድር ቢያብር አንበሳ ያስር የአባቶቻችን መሪ ቃል ነው። በዚህ የተነሳ በዕድር፣ በማህበር እና፣ በዕቁብ ተሳስረው በጋራ ማኅበራዊ ኑሮአቸውን እየመሩ ችግራቸውን ይቀርፉ ነበር። እኛም በሰሜን አሜሪካ፣ በካሊፎርኒያ ግዛት፣ በሳንሆዜ አካባቢ የምንገኝ ኢትዮጵያዊያንና ኢትዮ-አሜሪካዊያን ለብዙ ጊዜ የምንመኘውን ይህን ዕድር አቋቁመናል። ዕድራችንን ማዳበር፣ ኅብረታችንን ማጠናከር የሁላችንም ኃላፊነት ነው።

ሚያዝያ 27 ቀን 2017 ዓ.ም (May 5, 2025)

# የኢትዮጵያውያን አንድነት ዕድር መተዳደሪያ ደንብ

## መ ግ ቢ ያ

እኛ በሰሜን አሜሪካ በካሊፎርንያ ግዛት በሳንሆዜና አካባቢው ከተሞች የምንገኝ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮ -አሜሪካውያን ለብዙ ጊዜ ስንመኘው የነበረውን የመረዳጃ ዕድር አቋቁመናል። ዕድር ለተለያዩ አገልግሎቶች በተለያየ መልክ እየተመሰረተ ሲያገለግል የኖረ ባህላዊ እሴታችን ነው። ይህም እንደየተግባሩ በመተዳደሪያ ደንብ ይገለጻል።

አሁንም የእኛ ዕድር አላማውና ተግባሩ ከታች እንደሚያስረዳው አንድ መብትና ግዴታውን ያሟላ አባል በራሱም ሆነ በቤተሰቡ ላይ የሞት አደጋ በሚደርስበት ጊዜ ዕድሩ ፈጥኖ በመድረስ ደንቡ በሚፈቅደው መሠረት የገንዘብ፤ የሃሳብና ሌሎች ማህበራዊ ድጋፎችን ለማድረግ የተቋቋመ ነው።

ይህ ከአንቀጽ 01 እስከ አንቀጽ 17 የተካተተ ደንብ የኢትዮጵያውያን አንድነት ዕድር መተዳደርያ ደንብ ሆኖ ያገለግላል።

## ክፍል አንድ

## ትርጉም

1. ዕድር ማለት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሞት አደጋ በሚደርስበት ወቅት በገንዘብና በሞራል ለመረዳዳት የተቋቋመ ማሕበራዊ አገልግሎት መስጫ ነው።

2. ዕድርተኛ ማለት የዕድሩን ሕግና ደንብ ተቀብሎ አባል የሆነ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ነው።

3. ቤተሰብ ማለት ባል ሚስት እና እስከ 21 ዓመት ድረስ ያሉ ልጆችን ያካትታል።

4. ባልና ሚስት ማለት በሕግ ተጋብተው ሳይፋቱ በአንድ አድራሻ የሚኖሩና በዕድሩ ማመልከቻ ላይ ስማቸው የተጠቀሰው አባላት ናቸው።

5. ልጆች ማለት እድሜያቸው እስከ 21 ዓመት የሆኑ ከወላጆቻቸው ጋር አብረው የሚኖሩና በማመልከቻው ላይ የተጠቀሱትን ያካትታል።

6. እንግዳ ማለት በማንኛውም ጊዜ ከሌላ አካባቢ ለጉብኝት ወይም ለጥየቃ መጥቶ በዕድርተኛው መኖሪያ ቤት እስከ ስድስት ወር የሚቆይ ጊዜያዊ ነዋሪ ማለት ነው ከስድስት ወር በላይ በዕድርተኛው አድራሻ የሚቆይ ከሆነ ግን እንግዳ አይባልም። ይህም ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ እድሩ ማስረጃ ሊጠይቅ ይችላል።

7. በወንድ ጾታ የተገለጸ ሁሉ ለሴትም ያገለግላል።

## ክ ፍ ል ሁለት

## የዕድሩ መገለጫዎች

## አንቀጽ 1 - ስያሜ

1.1 ዕድሩ የኢትዮጵያውያን አንድነት ዕድር ተብሎ ይጠራል።

## አንቀጽ 2 - የዕድሩ አድራሻ

2.1 የዕድሩ አድራሻ በካልፎርንያ ግዛት በሳንታ ክላራ ካውንቲ ሳንሆዜ ከተማ ነው።

## አንቀጽ 3 - የዕድሩ ዓላማ

3.1 በሳንሆዜና አካባቢዋ የምንኖር ኢትዮጵያዊያንና ኢትዮ-አሜሪካውያን አገር በቀልና ፍቱን በሆነው ባህላችን በዕድር ተደራጅተን በሞት አደጋና በቀብር ጊዜ በሀሳብ በገንዘብና በጉልበት ለመረዳዳት፤

3.2 ዕድርተኛው ወይም ባለቤቱ እንዲሁም ልጆቹ በጸና ታመው ራሳቸውን ለመርዳት ከአቅም በላይ የሆነ ደረጃ ሲደርሱ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ለመጠየቅና አስፈላጊውን ትብብር ለማድረግ፤

3.3 ዕድርተኛው የሟቹ አስከሬን ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄድ ከወሰነ ደንቡ በሚፈቅደው መሰረት አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ፤

3.4 የሚረዳዳና የሚተሳሰብ ማህበረሰብ ለመገንባት የሚያስችሉ ተግባራትን ሁሉ ለማከናወን፤አግባብ ካላቸው አካላት ጋር ተገቢውን ለመፈጸም፤

3.5 አገር በቀል የሆነውንና ለረጅም ዘመን የተፈተነውን ባህላችንን ለልጆቻችን ለማስተላለፍ፣ ጠንካራና ጤናማ ቤተሰብ ለመመስረት ነው።

## አንቀጽ 4 - የዕድሩ ሕጋዊ ሰውነት

4.1 በካሊፎርንያ ግዛት ሕግና ደንብ መሠረት ፈቃድ ከአገኘበት ጊዜ ጀምሮ የራሱ ሕጋዊ ሰውነት አለው።

4.2 ይህ ዕድር በአባላቱ መዋጮና ከልዩ ልዩ እርዳታ ሰጪዎች በሚገኘው ገቢ ይተዳደራል። አትራፊ ያልሆነ (Non Profit) ድርጅት ሆኖ ይቀጥላል።

4.3 ከዚህ በላይ የተጠቀሰው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውንም ውል ይዋዋላል፤ ይከሳል፤ ይካሰሳል፤ ንብረትና ገንዘብ ያስተዳድራል::

4.4 ይህ ደንብ የመንግስትን ሕግጋት በማይጻረር ሁኔታ ወይም የመንግስት ሕግና ደንብ የሚያዘውን ተከትሎ እንቅስቃሴውን ለማድረግ የተዘጋጀ ነው።

## አንቀጽ 5 – የዕድሩ የገቢ ምንጮች

5.1 ከአባላት መመዝገቢያ እና ወርሀዊ ክፍያ

5.2 የዕድሩ አባላት በሚፈጥሩት ልዩ ልዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ምንጮች ማለትም ከግለሰቦችና ከድርጅቶች ወዘተ የሚገኘው ይሆናል።

# ክ ፍ ል ሦስት

## አንቀጽ 6 - አባል ስለመሆን

6.1 ዕድሩ የዘር፤ የሃይማኖት፤ የቀለም፤ የጾታና የፖለቲካ ልዩነት አያደርግም።

6.2 እድሜው 18 ዓመትና ከዚያም በላይ የሆነ ማንኛውም የካሊፎርንያ ግዛት መታወቂያ ያለው/ያላት አመልካች የዕድሩ አባል ለመሆን ጥያቄውን በተዘጋጀው ቅጽ ሞልቶ ሲያቀርብ።

6.3 የዕድሩን መተዳደሪያ ደንብ አምኖ የተቀበለና ዕድሩ የሚጠይቀውን መረጃዎች ካቀረበ በኋላ ዕድሩ ተገቢዉን ማጣራት አድርጎ አጥጋቢ ሆኖ ካገኘው በአባልነት ይመዘገበዋል ፤ የአባልነት መታወቂያም ይሰጠዋል።

6.4 የዕድሩ አዲስ አባል ለመሆን የመመዝገቢያ $300.00 (ሦስት መቶ ዶላር) እና ወርሃዊ መዋጮ ይከፍላል። የጥቅሙ ተከፋይ ለመሆን አንድ ዓመት መጠበቅ አለበት።

6.5 አንድ ዕድርተኛ የተለያዩ የአባልነት መብቶቹ የሚጠበቁለት፤ ለአስራ ሁለት ወራት (ለአንድ ዓመት) ክፍያዎችን አጠናቆ በተከታታይ ሲከፍል ነው።

6.6 እድሜያቸው ከ21 አመት በላይ የሆኑ የእድሩ አባል ልጆች በግል አባል መሆን ከፈለጉ በቤተሰብ የሚያገኙት የእድሩ ጥቅም በተቋረጠ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ያለምንም የመመዝገቢያ ክፍያ የወርሃዊ ክፍያ ብቻ በመክፈል በግላቸው የእድሩ አባል በመሆን ያለምንም የመጠበቂያ ጊዜ ሙሉ ተጠቃሚ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 7 - የምዝገባ ሥነ-ሥርዓት

ማንኛውም አመልካች የዕድሩ አባል ሆኖ ለመመዝገብ ከዚህ በታች የተዘረዘረውን በመጀመሪያ አሟልቶ መገኘት አለበት።

7.1 ማንኛውም በካሊፎርንያ ግዛት የሚኖርና የነዋሪነት መታውቂያ ካርድ ያለው አባል መሆን ይችላል።

7.2 የዕድር አባልነት መጠየቂያ ቅጾችን ሞልቶ በአካል ቀርቦ ማስገባት አለበት

7.3 ማንኛውም አዲስ አባል በአባልነት ሲመዘገብ የራሱንና የቤተሰቡን አባላት መታወቂያና ሌሎችም አስፈላጊ መረጃዎችን ማቅረብ አለበት።

7.4 ዕድሩ አጠራጣሪ መረጃዎች ቀርበውለት ትክክለኛነቱን ካላመነበት አመልካቹን ለመቀበል አይገደድም።

## አንቀጽ 8 - መብት

8.1 አንድ ዕድርተኛ የመምረጥና ድምጽ የመስጠት መብት ሲኖረው ለመመረጥ ግን አንድ አመት ዕድሩ ውስጥ መቆየት ይኖርበታል።

8.2 አንድ ዕድርተኛ አባል ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ሃሳቡን በነጻነት የመግለጽ መብት አለው

8.3 - አንድ ዕድርተኛ ሙሉ የአባልነት መብቱ የሚጠበቅለት፤ ለአስራ ሁለት ወራት (ለአንድ ዓመት) ክፍያዎችን አጠናቆ መክፈሉ ሲረጋገጥ ነው።

8.4 አንድ አባል 12 ወር በአባልነት ከቆየ በኋላ በደንቡ መሠረት ባስመዘገባቸው ቤተሰቦች ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ ደንቡ የሚፈቅደውን ማንኛውንም ጥቅም የማግኘት መብት አለው።

8.5 አንድ የዕድር አባል ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ እንደ አባሉ ፍላጎት የቀብር ሥነ ስርዓቱን ለማስፈጸምም ሆነ አስከሬኑን ወደ ሐገር ቤት የሚላክበትን ወጪ ለመሸፈን ይረዳ ዘንድ አባሉ ዕድር ውስጥ የቆየበት ጊዜ ታይቶ ከዚህ የሚከተለው ክፍያ ከዕድሩ ሂሳብ ወጪ ሆኖ ይከፈላል። ወደፊት የክፍያው መጠን እንደ አስፈላጊነቱ በጠቅላላ ጉባዔው ሊለወጥ ይችላል።

8.5.1 የዕድሩ አባል አንድ ዓመት ያልሞላው ከሆነና ባስመዘገባቸው ቤተሰቦቹ ላይ የሞት አደጋ ቢደርስ

- ዕድሩ ለአባላቱ መልዕክት ይተላለፋል።
- የዕድሩ አባላት ቤተሰቡን እንዲያጽናኑ፤ የቀብር ወይም ሸኝት ቦታ እንዲገኙ ዕድሩ ያስተባብራል።

- ሃሳባቸውን በነጻ መግለጽና መምረጥ ይችላሉ።

8.5.2 የዕድሩ አባል ከ1 (አንድ) ዓመት በላይ እና ከ2 (ሁለት) ዓመት በታች ከሆነው

- በቁጥር 8.5.1 የተጠቀሱትን መብቶች በሙሉ
- አሳባችውን በነጻ መግለጽ፤ መምረጥ እና መመረጥ ይችላሉ።
- የቀብር ስርዓቱን ማስፈጸሚያ $10,000 ይከፈላል።

8.5.3 የዕድሩ አባል ከ2 (ሁለት) ዓመት በላይ እና ከ3 (ሶስት) ዓመት በታች ከሆነ

- በቁጥር 8.5.2 የተመለከተው እንዳለ ሆኖ የቀብር ስርዓቱን ማስፈጸሚያ $15,000 ይከፈላል።

8.5.4 የዕድሩ አባል ከ3 (ሶስት) ዓመት በላይ ከሆነ

- በቁጥር 8.5.2 የተመለከተው እንዳለ ሆኖ የቀብር ስርዓቱን ማስፈጸሚያ $20,000 ይከፈላል።

| ከ**1** (አንድ) ዓመት ያነሰ | ከ**1** (አንድ) ዓመት በላይ እና ከ**2** (ሁለት) ዓመት በታች | ከ**2** (ሁለት) ዓመት በላይ እና ከ**3** (ሶስት) ዓመት በታች | ከ **3** (ሶስት) ዓመት በላይ |
|---|---|---|---|
| ለዕድር አባሎች መልዕክት ይተላለፋል | ለዕድር አባሎች መልዕክት ይተላለፋል | ለዕድር አባሎች መልዕክት ይተላለፋል | ለዕድር አባሎች መልዕክት ይተላለፋል |
| የዕድር አባላቶች ቤተሰብ ያጽናናሉ | የዕድር አባላቶች ቤተሰብ ያጽናናሉ | የዕድር አባላቶች ቤተሰብ ያጽናናሉ | የዕድር አባላቶች ቤተሰብ ያጽናናሉ |
| | መምረጥ እና መመረጥ ይችላል | መምረጥ እና መመረጥ ይችላል | መምረጥ እና መመረጥ ይችላል |
| | ለቤተስብ $10,000 በሰው ይከፈላል | ለቤተስብ $15,000 በሰው ይከፈላል | ለቤተስብ $20,000 በሰው ይከፈላል |

## የገንዘቡ አከፋፈል

ሀ. ባል ከሞተ ለሚስት

ለ. ሚስት ከሞተች ለባል

ሐ. ማመልከቻው ላይ ለተጠቀሰ አካል (Beneficiary)

መ. ማመልከቻው ላይ የተጠቀሰ አካል ከሌለ በአንቀጽ 9.13 በተገለጸው መሰረት ይፈጸማል

8.6 በአንድ የዕድር አባል መኖሪያ አድራሻ በእንግድነት ያለ ሰው ላይ የሞት አደጋ ሲያጋጥም እንግዳው ባረፈበት አድራሻ ላለው የማህበር አባል ብቻ $2,000.00 ዶላር ይሰጠዋል። ይህ ማለት ለአንድ ክስተት አንድ ክፍያ ብቻ ይፈጸማል።

8.7 አንድ ዕድርተኛ የአባልነት የወር ክፍያውን ለመክፈል ለጊዜው በሕመም ሆነ በተለያዩ የግል ችግሮች ምክንያት የወር ክፍያውን መክፈል እንዳልቻለ ለቦርዱ በጽሑፍ ካስታወቀና ቦርዱም የአባሉን ጥያቄ አጥንቶና ተወያይቶበት ለጊዜው መክፈል አለመቻሉን ካረጋገጠ በኋላ አባልነቱን እስከ አንድ ዓመት ያህል በነጻ ሊቀጥል ይችላል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ችግር ቢያጋጥመው በደንቡ መሰረት እርዳታውን ወይም ክፍያውን ያገኛል። ቦርዱም ጉዳዩን ለጠቅላላ ጉባዔ ያሳውቃል።

8.8 አንድ አባል ከ8.7 ከተገለጸው ውጪ ከአንድ አመት በላይ ገቢ እንደሌለው ከተረጋገጠ ቦርዱ ሁኔታውን አጥንቶ አባሉ ከአንድ ዓመት በላይ ካለ ክፍያ እንዲቀጥል አስፈላጊውን መረጃ ለጠቅላላው ጉባዔ አቅርቦ ያጸድቃል።

8.9 አንድ ያላገባ አባል በሞት ቢለይ ማመልከቻው ላይ የተገለጸው ተወካይ (Beneficiary) አባሉ ከአረፈ በኋላ እስከ 6 ወር (ስድስት ወር)ከተመዘገበ ያለመመዝገቢያ ክፍያ በዕድሩ እንደ አዲስ አባልነት ለመቀጠል መብት ይኖረዋል። ይህ አዲስ አባል ጥቅም ማግኘት የሚችለው በአንቀጽ 8.5 በተጠቀሰው መሰረት ይሆናል።

8.10 አንድ የቅርብ ቤተሰብ ማለትም በወንድሞችና እህቶች የዕድር አባላት መካከል የጋራ ዘመድ የሞት አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ በሕገ ደንቡ ላይ የተጠቀሰው እርዳታ የሚሰጠው በአንቀጽ 8.6 በተደነገገው መሠረት ነው።

8.11 የዕድሩ አባል የነበሩ ባልና ሚስት ከተፋቱ ሁለቱም በየስማቸው አዲስ የአባልነት ማመልከቻ በመሙላት በአባልነታቸው መቀጠል ይችላሉ። በዚህም ሁኔታ ተጨማሪ የመመዝገቢያ ክፍያ አይጠየቁም። አባላቱ ከተፋቱ በስድስት ወር ወስጥ እንደ አዲስ ከተመዘገቡ የዕድሩን ሙሉ ጥቅም ያለምንም የመቆያ ጊዜ ያገኛሉ።

8.12 አንድ አባል በሥራ ወይም በሌላ ጉዳይ ወደ ሌላ አካባቢ ቢዛወር በወኪል አማካኝነት አባልነቱን ሊቀጥል ይችላል።

8.13 አንድ አባል በዕድርተኛነት መቀጠል ካልፈለገ የማቆም መብቱ የተጠበቀ ሲሆን ጥያቄውን እስካቀረበበት ቀን ድረስ ለአባልነት የከፈለው ገንዘብ አይመለስለትም። ይሁን እንጂ የስድስት ወራት ቅድሚያ የከፈለ አባል በመሃከሉ ከእድሩ ለመሰናበት ቢጠይቅ የአገልግሎት 20% ተቀንሶ ቀሪው ይመለስለታል። የአመት ክፍያ ከሆነና ጥያቄውን ያቀረበው በመጀመሪያው ክፍያ ውስጥ ከሆነ ግን የሁለተኛው ስድስት ወር በሙሉ ይመለስለታል።

8.14 አንድ አባል በማንኛውም ምክንያት ወደሌላ አካባቢ ሄዶ ቢሞት ለመሞቱ ሕጋዊ ማስረጃ እስከቀረበ ድረስና የሚጠበቅበትን የአባልነት ግዴታ አሟልቶ እስከተገኘ ድረስ ክፍያው ማመልከቻው ላይ ለተጠቀሰው ተወካይ (Beneficiary) ይሰጣል።

8.15 አንድ አባል አካበቢውን ለቆ ወደ ሌላ ከተማ፤ ግዛት ከሄደና በደንቡ መሠረት ክፍያውን ከቀጠለ የአባልነት መብቱ ይጠበቅለታል ሆኖም ግን በአንቀጽ 9.11 እና 9.12 የተጠቀሰውን ለማድረግ አይገደድም አባላቱም ለእርሱ አይገደዱም።

# አንቀጽ 9 - ግዴታ

9.1 የዕድሩ ደንብ የሚጠይቀውን ግዴታዎች መፈጸም።

9.2 አስገዳጅ ሁኔታ ካላገጠመ በስተቀር በጠቅላላ ስብሰባ ላይ መገኘት።

9.3 ለመጀመሪያ ጊዜ መመዝገቢያ ዕድርተኛው $300.00 (ሦስት መቶ ዶላር) ይከፍላል።

9.4 የአባልነት ወርሃዊ ክፍያ በወር $30.00 (ሰላሳ ዶላር) ሲሆን ክፍያው በአመት ሁለት ጊዜ ብቻ ማለትም የመጀመሪያውን ከጃንዋሪ 1 እስከ ጃንዋሪ 31 ድረስ ያለ ቅጣት $180.00 ዶላር እንዲሁም ሁለተኛውን ከጁላይ 1 እስከ ጁላይ 31 ድረስ ያለቅጣት $180.00 ዶላር እንዲከፈል ወይም የአመቱን በአንድ ጊዜ ከጃንዋሪ 1 እስከ ጃንዋሪ 31 ድረስ $360.00 ዶላር እንዲከፈል ሲሆን ነገር ግን ከተቀመጠው ቀነ ገደብ ያሳለፈ አባል ማለትም ከፌብሩዌሪ 1 ወይም ከኦገስት 1 በኋላ በተጨማሪ $50.00 ዶላር ቅጣት ጋር ይከፍላል።

9.5 ክፍያውን በተወሰነው ጊዜ የማይከፍል አባል $50 መቀጫ ይከፍላል ነገር ግን ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ለምሳሌ ያህል በሆስፒታል ተኝቶ፤ እስር ቤት ገብቶ፤ በአዕምሮ በሽታ ታውኮ ከሆነ መቀጫውን እንዳይከፍል ይቅርታ ይደረግለታል ይህም ሊሆን የሚችለው በቂ ማስረጃ ሲያቀርብ ብቻ ነው።

9.6 በአንቀጽ 9.5 የተጠቀሰው ችግር ሳያጋጥመው የስድስት ወር ክፍያውን ሳያሟላ አንድ አደጋ በዕድርተኛው ወይም ቤተሰቡ ላይ ቢደርስ በሕጉ መሠረት የተመደበውን ክፍያና እርዳታ ማግኘት አይችልም።

9.7 እያንዳንዱ አባል መዋጮውን በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ አጠናቆ የመክፈል ግዴታ አለበት፡:

9.8 አንድ ዕድርተኛ የአባልነት መብቱ የሚጠበቅለት፤ ለአስራ ሁለት ወር (ለአንድ ዓመት) ክፍያዎችን አጠናቆ በተከታታይ ሲከፍል ነው። ክፍያውም በአንቀጽ 8.5 በተመለከተው መሰረት ነው፡፡

9.9 የአባልነት ጥያቄ አቅርቦ ተቀባይነት ያገኘ አባል በእየጊዜው ራሱንና ቤተሰቡን የሚመለከቱ ለውጦች ሲኖሩ ለዕድሩ የተዘጋጀውን የመመዝገቢያ ቅጽ እየሞላ ማሳወቅ አለበት።

9.10 በዕድርተኞች መካከል መቀራረብ፣ መፈቃቀር፣ መተሳሰብና መረዳዳት እንዲሰፍን እያንዳንዱ አባል አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ይጠበቅበታል።

9.11 አንድ አባል ሲሞት ዕድርተኞች የሚቹን ቤተሰብ የማስተዛዘን፤ የማስተባበር፤ የመቅበር ወይም የመሸኘት ግዴታ አለባቸው፡፡

9.12 አስከሬኑን ለመቅበር ወይም ወደ ሌላ ቦታ ለመሸኘት በሚደረገው ሥርዓት ላይ ዕድርተኞች በሙሉ በሃዘንተኛው ቤት ወይም በሚገለጸው ቦታ በመገኘት ያጽናናሉ። ከሃዘንተኛው ቤተሰብም ሆነ ከቦርዱ የሚሰጣቸውን የሥራ ድርሻ /ፕሮግራም በኃላፊነት ይወጣሉ።

9.13 አንድ ቤተሰብ ወይም ወኪል የሌለው አባል በሚያርፍበት ጊዜ የዕድሩ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ደንቡ በሚያዘው መሠረት የቀብሩን ሥነ-ሥርዓት ይፈጽማል።

9.14 የዕድሩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ኃላፊነቱን ይወጣል።

## አንቀጽ 10 - ከአባልነት ማቋረጥ

10.1 ከዕድር አባልነቱ መልቀቁን በጽሁፍ ለአስተዳደር ቦርዱ አሳውቆ የተሰጠውን የዕድር አባልነት መታወቂያውን ሲመልስ።

10.2 ብቸኛ የነበረ ከሆነ ራሱ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ፤ ወይም ሁለቱም ባልና ሚስት ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩና ሕጋዊ ወራሽ ሳይኖራቸው ሲቀር።

10.3 በዚህ ደንብ መሠረት የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ሲወሰድበት።

10.4 አንድ አባል በተለያየ ምክንያት መኖሪያ ቦታውን ከለወጠና የአባልነት ክፍያውን ካቋረጠ፤ እንዲሁም በአንቀጽ 10.1 እና 10.3 የተጠቀሰው ከተፈጸመ ቀደም ብሎ የከፈለው ገንዘብ ይመለስልኝ ብሎ መጠየቅ አይችልም።

## አንቀጽ 11 - ወደ አባልነት ስለመመለስ

11.1 አንድ አባል እስከ ስድስት ወር ድረስ ያልከፈለ ከሆነ ክፍያውን ከአቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ያለበትን ዕዳ፤ የሚቀጥለውን ስድስት ወር ክፍያና መቶ ዶላር መቀጫ ጋር በሰላሳ ቀናት(30) ከፍሎ አባልነቱን መቀጠል ይችላል።

11.2 አንድ አባል ከ ስድስት ወር በላይ ያልከፈለ ከሆነ ከዕድሩ በገዛ ፈቃዱ እንደለቀቀ ይቆጠራል ሆኖም ግለሰቡ በአዲስ መልክ ወደ ዕድሩ ተመልሶ መግባት ከፈለገ የአስተዳደር ቦርዱ ማመልከቻውን በመመልከት ወደ አባልነቱ እንዲመለስ ሊፈቅድለት ይችላል ይህም ሲሆን ተጠቃሚ ለመሆን በአንቀጽ 6.4 በተደነገገው መሠረት አንድ ዓመት መጠበቅ ይኖርበታል።

11.3 የዕድሩን ሕግና ደንብ ተላልፎ የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ተወስኖበት የተወገደ ከሆነ ግን ወደ ዕድሩ የመመለስ እድል የለውም።

## ክ ፍ ል አራት

## አንቀጽ 12 - ድርጅታዊ አወቃቀር

ዕድሩ በሶስት የእርከን ደረጃዎች የተዋቀረ አደረጃጀትና በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ እንዲሁም በአስተዳደር ቦርድ ቀርቦ በጠቅላላ ጉባኤ የሚጸድቅ አምስት አባላት ያሉት የሕገ ደንብ ትርጉም፤ ማሻሻያና አማካሪ ኮሚቴ ይኖረዋል:: በዚህም መሠረት:-

- ጠቅላላ ጉባዔ
- የአስተዳደር ቦርድ
- አባላት
- ኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ
- የሕገ ደንብ ትርጉም፤ ማሻሻያና አማካሪ ኮሚቴ ይኖሩታል።

## 12.1 የጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ሐላፊነት

12.1.1 በማናቸውም የዕድሩ ጉዳዮች ላይ የአባላቱ ጠቅላላ ጉባኤ ከፍተኛው የስልጣን ዕርከን ነው። ጠቅላላ ጉባዔው፤ ዕድሩን በባለቤትነትና በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል።

12.1.2 የጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ በዓመት አንድ ጊዜ ይደረጋል። ልዩ ስብሰባ በአስተዳደር ቦርዱ ወይም 1/3 ኛው አባላት ከጠየቁ ይጠራል። ስብሰባውን የሚመራው የቦርዱ ሊቀመንበር ነው።

12.1.3 ጠቅላላ ጉባዔው የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴዎችን መርጦ የአስተዳድር ቦርድንና የቁጥጥር ኮሚቴ አባላትን በዲሞክራሲያዊ ሂደት ምርጫውን ያከናውናል።

12.1.4 አስመራጭ ኮሚቴውም ሥራውን እንደፈጸመ ወዲያውኑ ለጉባዔው ውጤቱን ያሳውቃል።

12.1.5 ከግማሽ በላይ (51%) አባላት የተገኙበት ጠቅላላ ስብሰባ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

12.1.6 ጠቅላላ ጉባዔው ተጠርቶ ምልዓተ ጉባዔው ካልሞላ ሁለተኛ ስብሰባ ተጠርቶ የሚገኙት አባላት ከ 1/3 ኛ በላይ ከሆኑ ምልዓተ ጉባዔው እንደተሟላ ይቆጠራል። እጅግ በጣም ወሳኝ ከሆኑ ማለት ከተራ ቁጥር (12.1.12 እስከ 12.1.15) በቀር በተገኙት አባላት በመነጋገር ውሳኔ ማሳለፍ ይችላሉ።

12.1.7 ጠቅላላ ጉባኤው ሰባት አባላት ያሉት የአስተዳደር ቦርድና ሶስት አባላት ያሉት የቁጥጥር እና የኦዲት ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል። በተጨማሪ ሶስት ተጠባባቂ የቦርድ አባላትንና አንድ ተጠባባቂ የቁጥጥር/ኦዲት ኮሚቴ አባል አስፈላጊ ሲሆን ባገኙት ድምጽ መሰረት በተተኪነት የሚያገለግሉ ይዘጋጃሉ።

12.1.8 ከአባላት ለሚመረጡት ሰባት የአስተዳደር ቦርድ አስራ አራት እጩዎች እና እንዲሁም ከአባላት ለሚመረጡ ሦስት የቁጥጥር /ኦዲት ኮሚቴ ስድስት እጩዎች ለምርጫ ይቀርባሉ ።

12.1.9 ዝምድና ያላቸው አባላት በአንድ ላይ በተመሳሳይ ወቅት የዕድሩ አመራር ውስጥ እንዲያገለግሉ አይደረግም።

12.1.10 የቦርዱንም ሆነ የኦዲት ኮሚቴውን ሪፖርት አዳምጦ ተወያይቶ ይወስናል።

12.1.11 የዕድሩ መተዳደሪያ ደንብ እንዲሻሻል ወይም እንዲለወጥ በ 2/3 የጉባዔው አባላት ሲጠየቅ ወይም ቦርዱ በቃለ ጉባዔ ተነጋግሮና ተስማምቶ ለጉባዔው ሲያቀርብ፤ ተሰብስቦ እንዲሻሻል የሕግ አርቃቂ ኮሚቴ መርጦ ከአስጠና በኋላ ሲቀርብለት በማረም ያጸድቃል።

12.1.12 የዕድሩን መተዳደሪያ ደንብ ለማሻሻል ወይም ለመለውጥ የአባላት 2/3ኛ ድምጽ ያስፈለጋል።

12.1.13 የዕድሩን የሥራ ማስኬጃ በጀት ያጸድቃል።

12.1.14 በተለያዩ ጉዳዮች የቀረቡለተን ሪፖርት አድምጦ እንደስፈላጊነቱ ውሳኔ የሰጣል።

12.1.15 የዕድሩን ሕጋዊ ሰውነትና አገልግሎቱን ለማቋረጥ የጠቅላላ ጉባዔው 3/4ኛ ድምጽ ያስፈልጋል።

## አንቀጽ 12.2- የአስተዳደር ቦርድ ሥልጣንና ሐላፊነት

12.2.1 የአስተዳደር ቦርዱ የዕድሩን ዓላማ ለማስፈጸም በዚህ ደንብ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ተገቢውን ሁሉ ይፈጽማል። ከቦርዱ አቅም በላይ የሆነ አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም ልዩ ስብሰባ ይጠራል። አስቸኳይ ጥሪ ያደረጋል፤ ተሰብስቦ ያነጋግራል፤ ይወስናል፤ ይፈቅዳል፤ የአባላትን አስተያይት ያስተናግዳል፤ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች መልስና ማብራሪያ ይሰጣል።

12.2.2 ከቦርዱ ስላጣንና ሐላፊነት በላይ የሆኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙት ተሰብስቦ በመነጋገር ለጠቅላላ ጉባዔው ሪፖርት ያቀርባል።

12.2.3 የሥራ አስፈጻሚው ያከናወናቸውን የሥራ ዘገባ ለቦርድ ስብሰባ ያቀርባል።

12.2.4 ደንቡ በሚሰጠው ስልጣንና ሐላፊነት መሠረት ዕድሩን የሚመሩ ሰባት አባላት ያሉት የአስተዳደር ቦርድ ይኖረዋል።

12.2.5 የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ሲሆን ምርጫው የሚከናወነው በየዓመቱ በመጋቢት ወር ይሆናል። በአንድ ዓመት ምርጫ ሶስት (3) ወይም አራት (4) አዳዲስ የቦርድ አባላቶች ይመረጣሉ።

12.2.6 አንድ የቦርድ አባል በተከታታይ ለሁለት የሥራ ዘመናት ብቻ በመመረጥ ሊያገለግል ይችላል።

12.2.7 አንድ የቦርድ አባል የሥራ ዘመኑን ሳይጨርስ አገልግሎቱን በማንኛውም ምክንያት ቢያቋርጥ ለቀሪው የሥራ ዘመን እስከሚቀጥለው የምርጫ ጊዜ የሚያገለግል ማሟያ ከተጠባባቂ የቦርድ አባላት መካከል ቦርዱ በከፍተኛ ድምጽ የተመረጠውን እንዲያገለግል ያደርጋል። ለጠቅላላ ጉባዔውም ያሳውቃል።

12.2.8 በማንኛውም የቦርድ አባላት ምርጫ ጊዜ የቦርዱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሆነ አባል ተመልሶ ለቦርድ አባልነት ቢመረጥ የወቅቱ ተመራጮች ከነባሮቹ ጋር በሚገናኙበት ጊዜ የሥራ ድልድሉ በአዲስ መልክ ይፈጸማል።

12.2.9 ለሁለት የሥራ ዘመን በተከታታይ ያገለገለ የቦርድ አባል በድጋሚ ለመመረጥ ቢያንስ ለአንድ የሥራ ዘመን (ሁለት ዓመት) መቆየት አለበት።

12.2.10 ከቦርድ አባላት መካከል ሦስት (3) የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል።

12.2.11 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የዕድሩን የእለት ከእለት ሥራ እንዲሰራ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ከቦርዱ ውክልና ይሰጠዋል።

12.2.12 ከፍተኛ አደጋ የደረሰበትን፤ በጠና የታመመ አባልን በመጎብኘት ቤተሰቡ የሚረጋጋበትን፣ የሚረዳበትን መንገድ መተለም ይኖርበታል።

12.2.13 የዕድሩን የሂሳብ ደረጃ ይከታተላል፤የዕድሩን የመክፈል አቅም ለማጎልበት የተለያዩ የገንዘብ ማሰባሰቢያ መንገዶችን ይተልማል፤ ተግባራዊ ያደርጋል። የዕድሩ ተቀማጭ ገንዘብ ለ10 (አስር) አባላት ለመርዳት ከሚችለው በታች ሲሆን አስቸኳይ ስብሰብ ይጠራል ወይም የዓመቱ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ሁኔታውን ያሳውቃል፤የአንድ ጊዜ ተጨማሪ መዋጮ እንዲደረግ በጠቅላላው ጉባኤ አስወስኖ ተግባራዊ ያደርጋል።

12.2.14 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አባላት የሚከተሉት ይሆናሉ

- ሀ. ሊቀ መንበር፤
- ለ. ምክትል ለቀ መንበር
- ሐ. ዋና ጸሐፊ ናቸው

## 12.3 - ሊቀ መንበር

12.3.1 ሊቀ መንበሩ በማንኛውም ጊዜ የዕድሩ ተጠሪ ነው።

12.3.2 የጠቅላላ ጉባዔውንና የቦርዱን ስብሰባዎች በሊቀ መንበርነት ይመራል።

12.3.3 ከዕድሩ ሂሣብ ሹም ጋር የዕድሩን ቼክ ይፈርማል፣ ሂሣብ ሹሙ በሌለበት ጊዜ ከዋና ጸሐፊው ጋር በመሆን በቼኩ ላይ ይፈርማል።

12.3.4 በኮሚቴው የሥራ ክንውን ሪፖርትና በወጪና ገቢ ደብዳቤዎች ላይ ይፈርማል።

12.3.5 በዚህ መተዳደሪያ ደንብና በጠቅላላ ጉባዔው ወይም የአስተዳደር ቦርዱ በሚሰጡት መመሪያ መሠረት ዕድሩን በሚመለከት በማንኛውም ጉዳይ ዕድሩን ይወክላል። ከውጭ አካላት ጋር ዕድሩን ወክሎ ይነጋገራል።

12.3.6 የጠቅላላ ጉባዔውንና የአስተዳደር ቦርዱን ውሳኔዎች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

12.3.7 በአስተዳደር ቦርዱ አባላት አመራርነት ልዩ ልዩ ንዑሳን ኮሚቴዎች ሲመሰረቱ ሥራቸውን ይቆጣጠራል፤ እገዛ ያደርጋል።

## 12.4 - ምክትል ሊቀ መንበር

12.4.1 ሊቀ መንበሩ በሌለበት ወይም መሥራት በማይችልበት ጊዜ የሊቀ መንበሩን ቦታ ተክቶ ከላይ የተዘረዘሩትን ሥራዎች ሁሉ ያከናውናል ። ሊቀ መንበሩ ያለው ስልጣን ሁሉ ምክትል ሊቀ መንበሩ ይኖረዋል ።

12.4.2 የሊቀ መንበሩ ረዳት በመሆን ዕድሩን ያገለግላል።

12.4.3 የዕድሩን አላማ ለማስፈጸም ያግዛሉ ተብለው በሚገመቱት ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ሁሉ ከሊቀ መንበሩ ጋር በመመካከር ወይም ሥራ አሥፈጻሚው ኮሚቴም ሆነ ቦርዱ በሚሰጡት ውክልና ይሰራል።

12.4.4 ንዑሳን ኮሚቴዎችን እንደአስፈላጊነቱ ይመሠርታል ለሥራቸውም መመሪያ ይሰጣል።

## 12.5 ዋና ጸሐፊ

የአስተዳደር ቦርድ ጸሐፊ የሚከተሉት ሃላፊነት ይኖሩታል።

12.5.1 የጠቅላላ ጉባዔውንና የአስተዳደር ቦርዱን ቃለ-ጉባዔ ይይዛል።

12.5.2 ከሰብሳቢው ጋር በመመካከር አጀንዳ ያዘጋጃል፤ መልዕክቶችንና የስብሰባ ጊዜዎችን ለአባላት በጽሁፍም ሆነ በሌላ መንገድ ያስታውቃል።

12.5.3 ወጪ መሆን የሚገባውን ገንዘብ በአስተዳደር ቦርዱ ስብሰባ ሲፀድቅ ለገንዘብ ያዡና ለሂሣብ ሹሙ በጽሁፍ ያሳውቃል።

12.5.4 ሊቀ መንበሩ ወይም ምክትል ሊቀ መንበሩ ከአቅም በሆነ ምክንያት ስብሰባው ላይ ካልተገኙ የአስተዳር ቦርዱን ስብሰባ ይመራል፡

12.5.5 የአባላትን መዝገብ ወቅታዊነት እየተከታተለ በመዝገብ ይይዛል።

12.5.6 ማንኛውንም የዕድሩን ሰነዶች፣ ማህተምና የፖስታ ሳጥን ቁልፍ ይይዛል።

12.5.7 ማንኛውንም በእጁ የሚገኙ የዕድሩ መዛግብት ቁጥጥር ኮሚቴው ለሥራ በሚፈልግበት ጊዜ በአግባቡ ማቅረብና ማስመርመር ይኖርበታል።

## 12.6 - የሂሳብና የንብረት ሹም

12.6.1 የዕድሩን የሂሳብ መዛግብትና ደረሰኞች ይይዛል።

12.6.2 ለአባላት በአደጋ ጊዜ የሚደረገውን ክፍያም ሆነ ሌላ የክፍያ ቼኮችን ከሊቀ መንበሩ ጋር ፈርሞ ያስረክባል።

12.6.3 የዕድሩን ሂሳብ ሪፖርት ያዘጋጃል ያቀርባል።

12.6.4 የማህበሩን የሂሣብ መዛግብትን፣ ቼኮችን፣ ደረሰኞችን የኦዲት ኮሚቴው በሚፈልግበት ጊዜ ያቀርባል። የሂሳብ መዝገቡንም ያስመረምራል።

12.6.5 የዕድሩን ሥራ ማስኬጃ በጀት ያዘጋጃል። ለቦርድ አቅርቦ ውይይት ተደርጎበት ወደ ጠቅላላ ጉባዔው ቀርቦ ሲጸድቅም በሥራ ላይ እንዲውል ከገንዘብ ያዥ ጋር ይሰራል።

12.6.6 ወጪዎች በደንቡ መሠረት ወጪ መሆናቸውን ይከታተላል።

12.6.7 የዕድሩ ንብረት በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ይከታተላል።

## 12.7 - ገንዘብ ያዥ

12.7.1 በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ለዕድሩ ገቢ ሊሆን የሚገባውን ገንዘብ በየጊዜው እየሰበሰበ በዕድሩ የባንክ ሂሳብ ያስገባል።

12.7.2 ገንዘብ ያዡ የሥራ አገልግሎት ዘመኑን ሲጨርስም ሆነ በሌላ ምክንያት ከቦታው ሲነሳ በእጁ ያለውን ገንዘብና ንብረት በኦዲተሮች አማካኝነት ለተተኪው ያስረክባል።

## 12.8 - የሕዝብ ግንኙነት ሀላፊ

12.8.1 በማንኛውም ዕድሩን በሚመለከት ሁኔታ የሚደረገውን የማስተዋወቅ ሥራ ከጽሕፈት ቤቱ ጋር በመተባበር ያከናውናል።

12.8.2 የአባላትን ችግርና ቅሬታ ይከታተላል ችግሩንም ለአስተዳደር ቦርድ በጽሁፍ ያሳውቃል።

12.8.3 የዕድሩን ዓላማ ለማስፈጸም ከሚያግዙ ተመሳሳይ ተቋማት ጋር ግንኙነት በመመስረት ጥቅምና እርዳታ የሚገኝበትን ሁኔታ ያጠናል። ለቦርዱም ሪፖርት በማቅረብ ዕድሩ በተሻለ ሁኔታ አገልግሎት የሚያገኝበትን መንገድ ያመቻቻል።

12.8.4 የዕድሩ አሰራር የሚቀላጠፍበት ሁኔታ አጠቃላይ ጥናቶችን እያደረገ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል።

12.8.5 ዕድሩ ከጋራ ዋስትና ወይም መድህን (Group Insurance) ተጠቃሚ የሚሆንበትን መንገድ አጥንቶ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል።

12.8.6 የዕድሩን ደህረ ገጽ (WebSite) የማቋቋሙን የማስተዳደሩንና የማሳደጉን ጥረት በኃላፊነት ይመራል።

12.8.7 የዕድሩን የዶሜይን ስም ያስመዘግባል ምዝገባውም እንዳያልፍበት በያዓመቱ አስፈላጊውን እድሳት ያደርጋል።

12.8.8 አግባብ ካላቸውና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ጠንካራና ጤነኛ ቤተሰብ ለመፍጠር የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል።

## 12.9 - የማኅበራዊ ጉዳይ ኮሚቴ

12.9.1 በአባላት ላይ የሐዘን ችግር በደረሰ ጊዜ ከሐዘንተኞች ጋር በቅርብ በመወያየት አስፈላጊውን መስተንግዶ ያደርጋል።

12.9.2 ስለቀብር ቦታ፣ትራንስፖርት፣ፖሊስና ስለመሳሰሉት ጉዳዮች ከመሰል ተቋማትና አገልግሎት ሰጭዎች ጋር ግንኙት በማድረግ አስፈላጊውን ጥናትና ክንውን ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

12.9.3 በሃዘኑ ቤት አስተናጋጆችን ይመድባል ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

## 12.10 - ኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ

ሦስት አባላት ያሉት የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ በጠቅላላው ጉባዔው ይመረጣል፡፡ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለጠቅላላው ጉባኤው ሲሆን የሚከተሉት ሐላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

12.10.1 በዓመት ሁለት ጊዜ የዕድሩን አጠቃላይ የአስተዳደር፤ የሂሣብና የንብረት ሁኔታ በመቆጣጣር ለጠቅላላ ጉባዔው ዝርዝር ዘገባ ያቀርባል፡፡

12.10.2 የማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት የሚፈጠሩ ችግሮችን በወቅቱ መፍትሄ እንዲያገኙ ያማክራል፡፡

12.10.3 የዕድሩ መተዳደሪያ ደንብ በትክክል መከበሩንና የታቀዱት በጀቶች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፡፡

12.10.4 በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የተመዘገቡትን መመሪያዎች በየደረጃው እየተመለከተ ሕገ-ደንቡ በትክክል መተግበሩን ይቆጣጠራል፡፡

12.10.5 ከጥፋትና ከስህተት በፊት በንብረት፣ በፋይናንስ አያያዝና አስተዳደር ላይ ሀሳብ ይሰጣል፡፡

12.10.6 ኮሚቴው መደበኛ የስብሰባ ቀናት ይኖሩታል፡፡ ቢያንስ በወር አንድ ቀን ይሰበሰባል፡፡ ይሁን እንጅ አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥምና ተጨማሪ ስብሰባ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በመነጋገር ይሰበሰባል፡፡

12.10.7 ኮሚቴው በፈለገው ጊዜ የዕድሩን ገንዘብ፣ንብረትና የአስተዳደር ቦርዱን አሰራር ይመረምራል፡፡

12.10.8 የኦዲትና የቁጥጥር ኮሚቴ የሥራ ዘመን ለሦስት ዓመት ሲሆን ምርጫ የሚከናወነው በመጋቢት ወር በጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ዕለት ይሆናል፡፡

## 12.11 – ኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ የሥራ ክፍፍል

12.11.1 ኮሚቴው ራሱ በመመራረጥ፤ አንዱን ሰብሳቢ፤ ሁለተኛውን ጸሐፊና ሶስትኛውን አባል በማድረግ ይመዳደባሉ፡፡

## 12.12 - ኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ሰብሳቢው ሃላፊነት

12.12.1 የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴውን ይወክላል፡፡

12.12.2 የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴውን ሪፖርት ሁሉም አብረው ያዘጋጁትን ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል፡፡

12.12.3 የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴን ስብሰባ ይመራል፡፡

## 12.13 - ኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ጸሐፊው ሃላፊነት

12.13.1 የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴን ስብሰባ ቃለጉባዔ ይይዛል፡፡

12.13.2 የአባላትን ስም ዝርዝርና ሰነድ ይይዛል፡፡

12.13.3 ከጠቅላላ ጉባዔውና ከአስተዳደር ቦርዱ ጋር የሚጻጻፏቸውን ሰነዶች በኮሚቴው ሥር መቀመጥ ካለባቸው በጥንቃቄ ያስቀምጣል፡፡

## 12.14 - የሕገ ደንብ ትርጉም፤ ማሻሻያና አማካሪ ኮሚቴ

12.14.1 ከዕድሩ አባላት በአስተዳደር ቦርዱ በብቃታቸው የተመረጡ አምስት አባላት ለጠቅላላ ጉባዔ ቀርበው ለአምስት ዓመታት ይመደባሉ።

12.14.2 አንድ ሰብሳቢ፤ አንድ ምክትል ሰብሳቢና አንድ ጸሐፊ፤ ሁለቱ ደግሞ አባላት በመሆን ተግባራቸውን ከአስተዳደር ቦርድ ጋር በመመካከር ያከናውናሉ። ስብሰባቸውን እንደአስፈላጊነቱ ያደርጋሉ።

12.14.3 ለክርክርና ልዩነት መንስኤ የሆኑ ደንቦችና መመሪያዎችን በመመርመር ሐሳብ ያቀርባሉ።

12.14.4 ሕገ ደንቡንና ትርጉሙን እንዲሁም ጥያቄ የሚያስነሱ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ የመፍትሔ ሐሳብ በማቅረብ ከአስተዳደር ቦርዱ ጋር ችግሩን ለመቅረፍ በቅርበት ይሠራሉ።

12.14.5 የገንዘብ: ንብረትና የሰው ኃይል አስተዳደርና አጠቃቀም መመሪያዎችን በመገምገም ለዕድሩ መጠናከር የሚበጁ ሐሳቦችን ያቀርባሉ።

12.14.6 ያጋጠሙ ጠቃሚም ሆነ አሉታዊ ክስተቶችን በመገምገም ሕገደንቡ የሚሻሻልበትን የረቂቅ ሐሳብ ያቀርባሉ።

12.14.7 ስለተግባራቸው ዓመታዊ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባሉ።

12.14.8 የአስተዳደር ቦርዱ የዕድሩን እንቅስቃሴ ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረገግና የተለየ ምክር በሚያስፈልገው ወቅት ከአባላት መካከል ቀደም ሲል በቦርድ ውስጥ ካገለገሉት አባላቱ አማካሪውቹን መርጦ ማስመደብ ይችላል።

# አንቀጽ 13 - የሥነ ሥርዓት እርምጃ

ግዴታውን ባልተወጣ አባል ላይ እንደየጥፋቱ መጠን የሚከተሉት እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

13.1 የስድስት ወር ክፍያ በተከታታይ ያልከፈለ የአባልነት መብቱ አይጠበቅለትም። የከፈለው ገንዘብ ወይም ያበረከተው ስጦታ አይመለስለትም።

13.2 የዕድሩን ተግባርና እንቅስቃሴ ሊጎዳ የሚችል አሉባልታና የማይገቡ ተግባራትን የሚያራምድ አባል ላይ የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ተወያይቶ የቃል ወይም የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

13.3 አንድ አባል በዕድሩ ስብሰባ ላይ ወይም የአስተዳደር ቦርዱ የሚያካሂደውን የዕድር ሥራ ለማደናቀፍ ሲሞክር ወይም በስውር ዕድሩን የሚጎዳ ሁኔታ ሲፈጽም በማስረጃ ከተረጋገጠ ቦርዱ ጉዳዩን መርምሮና ጥፋተኛ ሆኖ ሲያገኘው እንደጥፋቱ መጠን ለመጀመሪያ ጊዜ ቦርዱ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ጥፋቱን በግል ማህደሩ እንዲቀመጥ ያደርጋል። ለሁለተኛ ጊዜ ከ $50.00 (አምሳ ዶላር) መቀጫ ጋር ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል። ለሶስተኛ ጊዜ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ግን ከዕድር አባልነቱ ይሰናበታል። የከፈለውም ገንዘብ ወይም ያበረከተው ስጦታ አይመለስለትም።

13.4 በዕድሩ ላይ የማጭበርበር የእምነት ማጉደል ተግባር ፈጽሞ የተገኘ አባል ድርጊቱ በማስረጃ ከተረጋገጠበት የከፈለው ገንዘብ ሳይመለስለት ይሰናበታል። ከዕድሩ በማናቸውም ምክንያት ለሥራ የወሰደውን ንብረትም ሆነ ገንዘብ ይመልሳል እንዲሁም ይህንን ጉዳይ ለማስፈጸም ዕድሩ ያወጣው ወጪ (ገንዘብ) ካለ የመክፈል ግዴታ አለበት።

# <u>ክፍል አምስት</u>

## አንቀጽ 14 የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት

14.1 በማንኛውም ምክንያት ቅሬታ ያለው የዕድሩ አባል ወይም አባሎች ቅሬታቸውን እንደክብደቱ ለሊቀ መንበሩ ወይም ለአስተዳደር ቦርዱ በጽሁፍ ያቀርባሉ። ሊቀ መንበሩ ወይም የአስተዳር ቦርዱም ከ 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

14.2 በአስተዳደር ቦርዱ ውሳኔ ያልተስማማ አባል ወይም አባሎች ጉዳዩ ለጠቅላላጉባዔ እንዲቀርብለት በጽሑፍ ይጠይቃል። ጠቅላላ ጉባዔውም እንደጉዳዩ ክብደትእንዲሁም በአመችነት በልዩ ስብሰባ ወይም በመደብኛ ስብሰባ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

14.3 ማንኛወም አይነት ቅሬታ የወንጀል ተገባር ካልሆነ በስተቀር ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 14.1 እና 14.2 በተመለከተው መሠረት ሳይፈጸም ወደ ውጭ የዳኝነት አካል ወይም አስማሚ አይቀርብም።

14.4 በዚህ ህገ ደንብ መሰረት ከአባልነት የተሰናበተ አባል ጉዳዩ እንደገና እንዲታይለት ለጠቅላላ ጉባዔው በጽሁፍ ይግባኝ የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ይሆናል።

## አንቀጽ 15 - አጠቃላይ ጉዳዮች

15.1 የዕድሩ ገንዘብ ፤ንብረት፤ቁሳቁስ በሙሉ በአግባቡ ተመዝግቦ ይያዛል።ብክነትና ጉዳት እንዳያገኛቸው ተገቢው ጥንቃቄ ሁሉ ይደረጋል። ይህንን ተግባር የሚያስፈጸመው የአስተዳደር ቦርዱ በጋራና ወይም በተናጠል የሥራ ድርሻቸው መሰረት ይሆናል።

15.2 ከሌሎች አካላት ማለትም መንግስታዊ፤ድርጅታዊና ግለሰባዊ ከሆኑ አካላት ጋር የሚደረግ ግንኙነት የዕድሩ የበላይ አካል የሆነው ጠቅላላ ጉባዔው ውክልና በሰጠው በአስተዳደር ቦርዱ ሊቀ መንበር ወይም እርሱ በወከላቸው ግለሰብ/ግለሰቦች ሊሆን ይችላል።

15.3 ከባንክ ጋር የሚኖር ግንኙነት፤ የዕድሩ ፀባይ ሁልጊዜ ከባንክ ጋር አብሮ መስራትን ይጠይቃል፤ ስለሆነም የፋይናንስን ጉዳይ በተመለከተ በሂሳብ ሹሙ ግንባር ቀደምትነት የሥራ አመራሩ ተግባራዊ መሆን አለበት። ገንዘብ ከባንክ ማውጣትን በተመለከተ ግን ደንቡ ከወከላቸው ከሁለቱ የሥራ አስፈጻሚ አባላት ጋር ካልሆነ በቀር ብቻውን ፈርሞ ማውጣት አይችልም።

15.4 ደንብን ማሻሻል (መለወጥ) የሚቻለው ሕጉ ከደረስንበት የእድገት ደረጃና ከካሊፎርኒያ ግዛት ሕግ ጋር የማይጣጣም ከሆነ ፤ የተፈለገውን ነገር ካላካተተ ወይም ሌላ አሳማኝ ሁኔታ ሲፈጠር ብቻ ነው።

15.5 ደንቡ ያላካተታቸውና መደረግ ያለባቸው ጉዳዮች ሲያጋጥሙ፤ ቦርዱ በቃለ -ጉባዔ ተነጋግሮ በድምፅ ብልጫ መወሰንና ችግሩን በጊዜያዊነት ለመፍታት መመሪያ ይሰጣል በመቀጠል ግን ለጉባዔው አቅርቦ ሕግ አርቃቂው እንዲያየውና ተስተካክሎ ሕግ ሆኖ በጉባዔው እንዲጸድቅ ይደረጋል።

15.6 አንድ የማንኛውም ኮሚቴ አባል በተለያዩ ምክንያቶች ከኮሚቴው አባልነቱ ሊለቅ ይችላል። ይህንንም ለኮሜቴው በጽሁፍ ካሳወቀ በኋላ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው። በተለያዩ የስነ-ሥርአት ከሆን ግን ፣ በሶስት አራትኛ የኮሜቴው አብላጫ ድምጽ ውሳኔ መሰረት ይሆናል።

15.7 በቡድን መከፋፈልና ችግር መፍጠር፤ በዕድሩ ሕልውና ላይ አደጋ የሚፈጥሩ ሁኔታዎች ሲከሰቱ የሥራ አመራር ኮሚቴው ፈጣን እርምጃ ይወስዳል። ግለሰቦቹን ያነጋግራል ወይም ተደማጭ የሆኑ የዕድሩ አባላትን በመምረጥና በማወያየት ችግሩን ማለሳለስና ማስወገድ አለበት። ከአቅሙ በላይ ከሆነ ለጠቅላላው ኮሜቴ ያሳውቃል።

15.8 የዚህ ደንብ የመግባቢያ ቋንቋ አማርኛ ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወደ እንግሊዝኛ ይተረጎማል:: በትርጉም መከከል ልዩነት ቢኖር በአማርኛ ቋንቋ የሰፈረው የፀና ይሆናል።

15.9 የዕድሩ የሂሳብ ዘመን (Fiscal Year) እ.ኤ አቆጣጠር ከጥር 01 እስከ ታህሳስ 31 (January 01 to December 31) ይሆናል።

15.10 በየዓመቱ መጨረሻ የገንዘብና የንብረት ቆጠራ በኦዲት ኮሚቴ ይደረጋል።

15.11 ይህ ደንብ ዕድሩ ከደረሰበት የእድገት ደረጃ እየተገመገመ ቢያንስ በ 1/3 ኛው የአባላት ጥያቄ እንዲሁም በሥራ እንቅስቃሴው ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ተጠንተው ለጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ ይሻሻላል ወይም እንዳስፈላጊነቱ ይከለሳል።

## አንቀጽ 16 - ዕድሩ የተቋቋመበት ጊዜና ቦታ

16.1 የኢትዮጵያውያን አንድነት ዕድር በካሊፎርንያ ግዛት ሳንታ ክላራ ካውንቲ በሳን ሆዜ ከተማ መስከረም 04 2007 ዓ.ም (SEPTEMBER 14/2014) ተመሠረተ። በዚህም መሰረት ዕድሩ በካሊፎርንያ ግዛት (State of California) አትራፊ ባልሆነ ድርጅትነት በቁጥር 3746223 የተመዘገበ ነው።

16.2 ይህ ደንብ የምንኖርበትን አገር ሕገ -መንግስት፣ ልዩ ልዩ ደንቦችን ሥርዓቶችን ያከበረና የተከተለ ነው።

## አንቀጽ 17 - ደንቡ የተሻሻለበት ጊዜ

17.1 ይህ ደንብ ለመጀመሪያ ጊዜ መጋቢት 10 ቀን 2010 ዓ.ም (March 17 /2018) ጸደቀ።

17.2 ይህ ደንብ ለሁለተኛ ጊዜ መጋቢት 23 ቀን 2015 ዓ/ም (April 01/2023) ተሻሻለ።

17.3 ይህ ደንብ ለሦስተኛ ጊዜ ሚያዝያ 27 ቀን 2017 ዓ/ም (May 5/2025) ተሻሻለ። በዚህ ደንብ ላይ የተሻሻሉት ህጎች ህጉ ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናሉ።